# <u>አልሞትክም ጥላሁን</u>

የዛሬው ሰማይ ያለወትሮው
የጸደይን ሕግ ጥሶ፡
የዳመናን ዓይን እየጨምቀ
አስኮርፎ አሰለቅሶ፡፡
ቀኑን ከጸሐይ አግልሎ፡
ቅፍፍ እንዳለ አውሎ፡
መርዶ አረዳኝ በማለዳ፡
ያላሰብኩትን ዱበዳ።
የጥላሁንን ዕጣ ፈንታ፡
የመጨረሻ ዝምታ፡
የዘላለሙን ሽልብታ።

ሀዘን በእጅጉ ቢሰማኝም፡
ሆዴ ባብቶ ቢላወሰም፡
እኔስ ከቶ ላንተ አላዝንም፡
ለጀግና ሰው አላለቅስም፡፡
ብዬ ከልቤ ተጽናንቼ፡
እንባዬን ባለበት ገትቼ፡
ወጣሁ አቀበቱን፡
ወረድኩ ቁልቁለቱን፡
ያለፈውን ዘመን
የደግ የክፉውን፡
ጥላሁን ገሰሰ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በዘፈን ነገሰ

የተባለበትን።

“ትዝ አለኝ የጥንቱ”

አወይ ሕይወት ከንቱ።

“በምሽት ጨረቃ”

“ሲሄድ ሲከተላት”

“እንጉዳዬ”እያለ እያወዳደሳት፡

እያጠያየቀ “ኩሉን”ማ እንደኳላት፡

“የዝናብ ማር” ብሎ እያቆላመጣት፡

ፍቅሩን ድብቅ አርጎ “ለብቻዬ”ብሎ፡

ሕይወትን ገለጻት

በደምጹ ዳሰሳት።

ጥላሁን ጥላችን

የመንፈስ ምግባችን፡

“ውበት የግዜር ጥበብ”

“መቼም አትጠገብ”።

“ካንድም ሁለት ሶሰቴ”

የኔ አካል በሞቴ፡

“እንደሞናሊዛ”

የቅላጼህ ለዛ፡

“ሩቅ ምሰራቅ “ሂዶ

ርቀቱን ንዶ፡

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይህው ቢናፍቀኝ፡

ፈገግታህ ቢያሞኘኝ፡

ጭሬ ዳመናውን

ጭጋጉን ዝናቡን፡

ከዳመናው በላይ፡ ዝናብ ካረገዘው፡

ከላይኛው ሰማይ፡ብርሃን ከለበሰው፡

አየሁህ ጥላዬ፡ ሞትን አናንቀህ፡

በጸሃይ ብርሃን፡አሸብርቀህ ደምቀህ።

ጥላሁን ጥላችን፡

ፍቅር መጋቢያችን፡

ያሳለፍከው ዘመን"ደሰታን ያየንበት"

"ተመልሶ ቢገኝ፡ አሁን ምናለባት"?

ከሻለቃ ለማ በላይነህ (አየር ኃይል)

ቨርጂኒያ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com